# "የማያድግ ህፃን አይርገምህ፣
# የማይሞት ሽማግሌ አይክዳህ!" አዲስ አባባል

## ይድረስ ለአቶ ኃይሉ ሻወል…

**ይህንን ደብዳቤ ካዘጋጀሁት በኋላ በስሜ ላወጣው ነበር። ነገር ግን በውስጡ ያለው ጭብጥ ከግለሰባዊነት ይልቅ፣ የህዝቡን አመለካከት የሚያንጸባርቅ በመሆኑ፣ ጉዳዩ በሚመለከተው የኢትዮጵያ ህዝብ ስም አቅርቤዋለሁ።**

**የኢትዮጵያ ህዝብ ድምፅ**

ታህሳስ 1 ቀን፣ 2007 ዓ.ም የጻፉትን ደብዳቤ፣ በቅድሚያ በወያኔ እና ፀረ-ቅንጅት በሆኑ ድረ ገጾች ላይ አንብበነዋል። በርግጥ በኋላ ላይ ሌሎች ድረ-ገጾችም አውጥተውት ተመለከትነው። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ የወሰዱት እርምጃ በአንድ በኩል፣ የቅንጅት መሪ ከሆኑ ግለሰብ መውጣቱ በጣም ያሳዝነናል። በሌላ በኩል ግን፣ የመጨረሻውን ጥይት ተኩሰው፣ ባንሞትም ገደሉን። ባይጎዱንም አቆሰሉን። በዚህ እርምጃዎ ግን የትግል መንገዱን አጠሩልን… እናመሰግንዎታለን።

እርስዎ በህዝቡ ላይ የጀመሩት ጥፋት የሚጀምረው ከአውራ ጎዳና መስሪያ ቤት ነው። በወቅቱ አንዲት ሴት የደርግ ባለስልጣን "ለምን ተናገረችኝ?" በሚል፣ በቅድሚያ አስተምሮ ለወግ ለማዕረግ ያበቃዎትን የኢትዮጵያ ህዝብ ትተው ወደ ባህር ማዶ ኮበለሉ። በወቅቱ የአውራ ጎዳና መስሪያ ቤት በሚሊዮን ብር እዳ ውስጥ እንዲገባ አድርገው ከቆዩ ከአስር አመታት በኋላ፣ አሜሪካ እያሉ በአቶ ፍቅረስላሴ ወግደረስ አማላጅነት እንደገና ከደርግ ጋር ለመስራት፣ ለምክትል ሚንስትርነት ማዕረግ ኮ/ል መንግስቱ ኃይለማርያምን እጅ ነስተው አገር ቤት ገቡ።

የደርግ ባለስልጣን በነበሩበትም ወቅት፣ አንድም የረባ ነገር ሳይሰሩ ቆይተው፣ "እንደገና ወደ ውጭ አገር መውጣት እፈልጋለሁ" በማለት ለኮ/ል መንግስቱ ኃይለማርያም ደብዳቤ በመጻፍ፣ ውጪ እንዲወጡ ከተፈቀደልዎ በኋላ፣ አሜሪካ ወጥተው… እንደወጡ ቀሩ። ከዚያም ወያኔ/ኢህአዴግ አዲስ አበባን ከተቆጣጠረ በኋላ፣ ስልጣን በመሻት መለስ ዜናዊ ጋር ለመቅረብ ያደረጉት ሙከራ ሳይሳካ ቀርቶ እንደገና ወደ አሜሪካ ተመልሰው፣ በሚኔሶታ ኑሮዎን ቀጠሉ። ከጥቂት አመታት በኋላ ደግሞ፣ ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ መአህድን አቋቁመው እየተንቀሳቀሱ በነበረበት ወቅት፣ ስልጣን ለመቀላወጥ አዲስ አበባ ተመልሰው በመምጣት፣ እንዳሰቡት የመአህድ ምክትል ሊቀመንበር ለመሆን ቻሉ፣ ስራዎትን… ይቅርታ ሴራዎትን ገፉበት።

የመጀመሪያው ሴራ ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስን በማሳጣት ከስልጣን ማስወገድና ወንበራቸውን መውሰድ ነበር። ወቅቱ ግርግር የነበረበት ስለሆነ፣ የወቅቱ የመአህድ ፕሬዘዳንት የነበሩት ፕ/ር አስራት ወልደየስ ነገሩን እንደተራ ጉዳይ በማየት ምህረት አደረጉልዎ። ሆኖም ከሳቸው ጀርባ በመሆን ይፈጽሙባቸው የነበረው በደል ታሪክ ይቅር የማይለው ሆነ። በተለይም በፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ላይ የተቃውሞ ደብዳቤ በመጻፍ፣ አምባገነን በማለትና በማሰኘት ተባበሩ። ፕሮፌሰሩን አምባገነን ማለትዎና ሌሎች ፀያፍ ቅጽሎችን በመጠቀም ከፍ ዝቅ አድርገው መሳደብዎ የትላንት ትዝታችን በመሆኑ፣ እርስዎም አይዘነጉትም።

በጣም የሚገርመው ግን በፕሮፌሰሩ ላይ ምስክር ሆነው መቅረብዎ ነው። ሻለቃ አድማሱና እርስዎ በተለያዩ ጊዜያት ማዕከላዊ ፖሊስ ድረስ በመሄድ፣ ሻለቃ አድማሱ በነአሰገደች ላይ እርስዎ ደግሞ ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ላይ ምስክርነትዎን እንደሰጡ ስንሰማ አዘንን። የውጭ ሰው እንዳይሰማ በሚል ነገሩን አፍነን ቆየን። በመሃል በዚሁ ተግባርዎ ዛሬም ቢሆን ከሚያውቋቸው ሰዎች፣ ከፍተኛ ተግሳጽ ሰለደረሰብዎ፣ "ለምን ታወቀብኝ?" በማለት፣ አኩርፈው ወደ ሚኒሶታ፣ አሜሪካ ተመለሱ። እርስዎ አሜሪካ ከገቡ በኋላ፣ የናንተን ምስክርነት መነሻ በማድረግ ኢህአዴግ "ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ በደብረ ብርሃን ጦር አደራጅተሃል" ተብለው ለመከሰስ በቁ።

አሜሪካ ሆነው ፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ በወያኔ እስር ቤት ውስጥ ሲማቅቁ፣ አንድ ቀን

እንኳ ሰላማዊ ሰልፍ ሳያስተባብሩላቸው፤ “እግዜር ይፍታዎ” ሳይሏቸው ቀሩ። ህመማቸው እየባሰ ሲመጣ፤ መለስ ዜናዊ እንኳን ለፕ/ር አስራት ወልደየስ ፈቃድ ሰጥቶ ውጪ እንዲታከሙ ሲፈቅድላቸው፤ እርስዎ ኤር-ፖርት ሄደው ሳይቀበሏቸው፤ አሜሪካ ካሉበት ሆስፒታል መጥተው ሳይጠይቋቸው፤ አንድ ቀን እንኳ “እግዜር ይማርዎ” ሳይሏቸው ህይወታቸው አለፈ (ጃኑዋሪ 1999)። በጣም የሚያሳዝነው የፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ማረፍ ብቻ ሳይሆን፤ አስከሬናቸው ከአሜሪካ ሲሸኝ፤ እርስዎ በስፍራው ጭምር ሳይገኙ መቅረትዎ ነው። በዚህ አላበቁም፤ በእኚህ ታላቅ ኢትዮጵያዊ፤ ፕ/ር አስራት ወልደየስ የቀብር ስነ ስርአት ላይ ለመገኘት እንኳን ሳይፈልጉ ቀሩ (ሜይ 26፣ 1999)። በዚህ ስላሴ ቤተክርስቲያን ቀብር ላይ የፕሮፌሰር አስራት አሳሪዎችና ደጋፊዎቻቸው ሳይቀሩ ተገኙ። ፓትሪያርኩ ጭምር በስፍራው ተገኝተው ፀሎተ ፍታት አደረጉ። እርስዎ ግን መገኘት ቀርቶ የሃዘን መግለጫ እንኳን ሳይልኩ ሰነበቱ። ይህም ምን ያህል ቂመኛ እና መጥፎ ሰው መሆንዎን በግልፅ አሳየን።

ይህ ብቻ አይደለም። ፕ/ር አስራት ወልደየስ ሞተው፤ አጥንት ጉልጥምታቸው ሳፈርስ፤ ሙት አመታቸው እንኳን ሳይከበር በመአህድ ውስጥ ምርጫ እንዲደረግና ያለምርጫ ፕሬዘዳንት ከሆኑ አዲስ አበባ እንደሚመጡ ተናገሩ። በ1999 ዓ.ም በመአህድ ውስጥ ምርጫ ተደረጎ፤ የፕሬዘዳንትነቱ ቦታ ለርስዎ ክፍት ተደረገ። ብዙም ሳይቆዩ በፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ አስከሬን ላይ ተረማምደው ሻንጣዎን ጠቅልለው እንደገና አዲስ አበባ ገቡ። የመአህድንም ቢሮ ተቆጣጥረው፤ በወቅቱ የመአህድ ፕሬዘዳንት የነበሩት ቀኛዝማች ነቅአ-ጥበብ በቀለ ላይ የማያዳግም እርምጃ እንዲወሰድ አድርገው፤ በሌሉበት የተመረጡበትን የፕሬዘዳንትነት ቦታ ተረከቡ። ምርጫ ቦርድም ይህንን አፀደቀልዎ፤ ቀጥለውም መአህድን አፍርሰው የመኢአድን መሰረቱ። ለምን መሰረቱ ብለን አንሞግትዎትም። ነገር ግን በዚያ ግርግር መሃል በርስዎ አምባገነናዊ እርምጃ ብዙዎች ተባረሩ። ቀኛዝማች ነቅአጥበብም በእርስዎ ድርጊት እንዳዘኑ ህይወታቸው አለፈ። የጨካኝነትዎ ጨካኝነት ቀኛዝማቹን ሳይቀብሩና ቤተሰቦቻቸውን ሳያጽናኑ ቀሩ።

በወያኔ እስር ቤት ለአምስት አመታት ከፕሮፌሰር አስራት ጋር፤ ሲማቅቁ የነበሩትን እነአቶ አሊ እድሪስ፣ እነ ወንዳየሁ ካሳና ሌሎችንም ከድርጅቱ በማባረር፤ ውለታቸውን በክህደት ከፈሏቸው። እዚህ ላይ ባለጉዳዮቹ እራሳቸውን መግለጽ የሚችሉ ስለሆነ፤ ጣልቃ በመግባት ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ አንገባም። በመኢአድ ውስጥ እያሉ፤ የተፈጠረውን ነገር ለታሪክ እንተወዋለን።

ሌላም በዝርዝር ልገባበት የማልፈልገው ነገር፤ የህብረቱ ጉዳይ ነው። “ህብረት” አሜሪካ ውስጥ ሲፈጠር፤ ምንም ስልጣን በማጣትዎ ህብረቱን ለቀው ሲወጡ፤ ራዕያችንን አጨለሙት። ቅንጅትን መስርተን ወደፊት ስንገሰግስ ደግሞ፤ አድብተው ወጉን… ግን አንሞትም።

የእርስዎን ተግባር፤ ከመአህድ እስከ መኢአድና ቅንጅት ፓርቲ ድረስ፤ ከዚያም እስከ እስር ቤት ድረስ የነበረውን ሁኔታ ብዙዎች ስለሚያውቁት በዚያ ላይ ጊዜ ማጥፋት ወይም ነገር መደጋገም አያስፈልግም። የምርጫውን ሰሞን ግን እናስታውስዎ።

በምርጫው ሰሞን፤ ለተቃዋሚዎች የሚዲያ እድል ሲሰጥ፤ እርስዎ አንድ ቀን እንኳ በቴሌቪዥን ቀርበው ኢህአዴግን ሳያወግዙ ወይም የኢህአዴግ ባለስልጣናትን ሳይሞግቱ፤ በሌሎች ትከሻ ላይ ተፈናጠው ታዋቂና ዝነኛ ለመሆን በቁ። ወቅቱ የግርግር በመሆኑ በፕሮፌሰር አስራትና በሌሎች ሰዎች ላይ የፈጸሙት በደል ተድበስብሶ፤ መጥፎ ተግባርዎ በቅንጅት ታድሶ፤ በሊቀ መንበርነት ሹመት የትላንቱን ረስተን ለአንድ አላማ አብረን ተሰለፍን። ዛሬ ላይ ሆነን ስናስበው ግን፤ “ለካስ ተሳስተን ነበር” ለማለት እየደፈርን ነው።

ከሁሉም በላይ የተሻለውን እድል ያገኙት ግን፤ የዛሬ ሁለት አመት ከስራ ይልቅ ጊዜዎትን ተፎካካሪ ፓርቲ ከሆነው ኢዴአፓ መድኅን ጋር ሲያጠፉ፤ በኋላም ከአቶ ልደቱ አያሌው ጋር ስም ሲጠፋፉ፤ የመኢአድ መስራቾችን ሲያባርሩ፤ ስለ እርስዎ ማንነት ህዝብ ለማወቅ እድል ሳያገኝ ቀረና ጊዜው በዋዛ ፈዛዛ አለፈ። እነ አቶ ልደቱን ከሃዲ ሲያስብሉ ቆይተው፤ ከእስር ቤት በኋላ እርስዎ ይበልጥ የተካኑበት መሆኑን አረጋገጡልን። በሚያሳቅቅ ሁኔታ የክህደትን ቁልቁለት

በዜሮ ማርሽ ወረዱት።

እራስዎ እንዲመሰረት ያደረጉትን "ቅንጅት አለም አቀፍ አመራር" በመንቀፍ፤ ከኢያሱ አለማየሁ የኢህአፓ ቡድን ጋር ሆኖ በአሜሪካ ከተሞች እየተዘዋወረ፤ እርስዎን ሲሰድብዎ የነበረውን ዶ/ር ታዬ ወልደሰማያትን ሾሙብን። ድሮ አዲስ አበባ እያሉ፤ ህይወትዎን ሊያጠፉ እንደነበር ደጋግመው ከሚመሰክሩባቸው የኢህአፓ መሪዎች ጋር አበሩና ቅንጅትን ለማጥፋት ደፋ ቀና ማለትን ቀጠሉበት።

ትላንት እውነት በመናገራቸው፤ ኮ/ል መንግስቱ ኃይለማርያም እንኳ እርምጃ ያልወሰደባቸውን፤ በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ አብረው ከጎንዎ ይተኙ የነበሩትን፤ ከጎንዎ አንድ አልጋ ላይ ተኝተው፤ "አይዞህ በርታ" ያሉዎትን፤ ዶ/ር ኃይሉ አርአያን ከድተው፤ "ከቅንጅት አግጄሃለሁ" ለማለት በቁ።

የአዲስ አበባ ቀጣና ኃላፊ በመሆን በመኢአድ ውስጥ ከፍተኛ ስራ የሰሩትን ብሩክ ከበደ እና ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራውን አግጃለሁ ብለው ለሁለተኛ ጊዜ አወጁ። ህዝብ ከዳር እስከዳር የደገፉቸውን፤ አለም ያከበራቸውን ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን በጥላቻ መንፈስ ኮንነው ሊያወግዟቸው ከጀሉ። ከእስር ከተፈቱ በኋላ፤ በየቀኑ እቤትዎ ድረስ በመምጣት ትጠይቅዎ የነበረችውን ብርቱካንን፤ አሜሪካ በተደረጉት ስብሰባዎች ላይ አንድም ቀን እርስዎን በክፋት ያላነሳችዎትን፤ "ጋሼ ኃይሉ እባክዎን ስሙኝ" በማለት እንባ እየተናነቃት፤ የተማጸነችዎን፤ አሁንም የእርቅ ኮሚቴ እንዲቋቋም አድርጋ ለእርቅ ደፋ ቀና ስትል የነበረችውን፤ ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳን ለማባረር አሰቡ… ከምክንያትዎ አንደኛው ደግሞ "HR2003 አይደግፉም" የሚል ውሸት መሆኑ፤ አንጀታችንን በጠሰው። ለርስዎ ያለንን እምነት ሰረዘው። አረ እንደው ምን አይነት ህሊና ነው ያለዎት?

በሰዎች ላይ የነበረዎን ጥላቻ በሚመለከት ብዙ ማለት ቢቻልም፤ በዚህ ደረጃ ቅንጅትና አመራሩን ለማፍረስ ይሰማራሉ ብለን አላሰብንም ነበር። አንድ ነገር ግን ላስታውስዎ። እርስዎ ምን ያህል ጉዳዩን እንደሚያስታውሱት ባላውቅም፤ በጁላይና ነሃሴ ወር 2005 ዓ.ም አሜሪካ መጥተው በነበረበት ወቅት፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ይካሄድ የነበረውን ጉዳይ እየተከታተልኩ፤ በእጅዎ ስልክና ያረፉበት ሆቴል ድረስ በመደወል እገልጽልዎ ነበር። ታዲያ ምን ጊዜም የማይረሳኝ ነገር፤ በወቅቱ በአቶ ልደቱ አያሌውና በዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ላይ የነበርዎ ጥልቅ የሆነ ጥላቻ ነው። ልደቱን መጥላትዎ አያስደንቀኝም። ሆኖም በአደባባይ፤ "አብረን እየሰራን ነው" እያሉ፤ በግል ጨዋታችን ግን ጥልቅ የሆነ ጥላቻዎን ሲገልጹልኝ ግራ ያጋባኝ ነበር።

በወቅቱ እኔ "ቅንጅት አዲስ አበባን መቆጣጠር አለበት" እያልኩ ፍላጎቴን በምክንያት ስገልጽልዎ፤ ያስጨነቀዎ ጉዳይ አዲስ አበባን መቆጣጠር ወይም ያለመቆጣጠር አልነበረም። ይልቁንም እርስዎን ቅር ያሰኘዎት፤ "ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ" ከንቲባ ሆኖ ከተማዋን መምራቱ እንደነበር ለመረዳት እድሉን አገኘሁ። አሁን ነገሩን ወደኋላ ተመልሼ ስመለከተው፤ እርስዎ የሚጨነቁት ለኢትዮጵያ ህዝብ ጥቅም ሳይሆን፤ ለራስዎ የግል ፍላጎት መሆኑን ከተረዳሁ አመታት ተቆጠሩ።

በ2005 አሜሪካ በነበሩበት ወቅት የሰሩት ቁም ነገር ቢኖር፤ እኛ ባዘጋጀናቸው የውጭ ሰዎች አማካኝነት ጋዜጣዊ መግለጫዎችን መስጠት ነበር። ታዲያ አንዳንዴ መግለጫ አሰጣጥዎ የተሳሳተ ፈር በመያዝ አንገታችንን የምንደፋበት አጋጣሚም ነበር። ያስታውሱ እንደሆነ፤ ከዚህ ቀደም እንግሊዛዊው ጋዜጠኛ "ለምን ቀደም ብለው በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ አልተሳተፉም?" ብሎ ሲጠይቅዎ፤ "ድሮ ልጆቼን አሳድግ ስለነበር ነው፤ ፖለቲካ ውስጥ ያልገባሁት!" በማለት መልስ መስጠትዎ ይታወሳል። እንግዲህ ኮትኩቼ አሳደኩ የሚሏቸው፤ አንደኛው አውሮፓ የሚገኘውና "አባቴ ታስሯል" እያለ በስምዎ ገንዘብ እየለመነ የነበረውንና ከነሻለቃ ዮሴፍ ገንዘብ እየተከፈለው ቅንጅትን ለማፍረስ ሲንቀሳቀስ የነበረውን አንተነህ ኃይሉን ነው። ስሜታዊ ሆኜ ወደ ቤተሰብ ጣጣ ውስጥ መግባት ስለማልፈልግ ነገሩን እዚህ ላይ ልተወውና አንድ ጥያቄ ልጠይቅዎ፤ "እርስዎ

ገደለ? የሚያሳዝነው፣ ዛሬም ከጥፋትዎ ሳይታረሙ፣ ከነዶ/ር ታዬ ወልደሰማያትና የቅንጅት ጠላቶች ጋር በመሆን በዚሁ ስራዎ ገፍተውበታል--- በአሳዛኝ መልኩ።

ይህ ብቻ አይደለም። በነዚህ በሞቱት ኢትዮጵያዊያን ደም ላይ ቆመው ቅንጅትንና አመራሩን ለማፍረስ በማሰብ፣ በቃሊቲ እስር ቤት ከእርስዎ ጋር የነበሩትን ሰዎች ጭምር ከስራ ለማገድ ያደረጉት ጥረት እጅጉን ያሳዝናል። ከምንም በላይ ደግሞ አሳዛኝ የሚሆነው፣ ከዚህ በፊት ለሰሩት ጥፋት ይቅርታ ሳይጠይቁ፣ በጥፋት ላይ ጥፋት በመጨመር፣ በቀጥታ ቅንጅትን በማፍረስ ተግባር ላይ ተሰማሩ። ስራና ተግባርዎን ደጋግመን ስናጤነው በእርስዎና በመለስ ዜናዊ መካከል ያለው ልዩነት አልገባ ብሎን የተቸገርን በጣም ብዙ ሰዎች ነን።

ሌላው ቢቀር... ቅንጅት የአስታራቂ ኮሚቴ አቋቁሞ እርስዎን ያለመታከት ሲለምንዎ ነበር። ይህንን አምባገነናዊ ደብዳቤ ከማውጣትዎ አንድና ሁለት ቀን በፊት ጭምር በየቀኑ ለሰአታት ሲያነጋግርዎ ቆይተዋል። የሚገርመው ነገር፣ በአንድ በኩል ለአስታራቂ ሽማግሌዎች ተስፋ እየሰጡ፣ በሌላ ወገን ደግሞ፣ የህዝብን ድምፅ በመናቅ፣ እንዲህ አይነት ውሳኔ ለመስጠት መቻልዎ ከአምባገነንነት በላይ መሰሪነትዎን በግልፅ የሚያሳይ ሆኗል።

ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ ሆኖ እንጂ፣ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የሚገኘው ኢትዮጵያዊ የርስዎ ነገር እየቀረጠለት መጥቷል። እንደምንሰማውም ከሆነ፣ በሽምግልና ስም ወደ አሜሪካ የላኳቸው፣ ጓደኞችዎ ሻለቃ አድማሱ እና ዶ/ር በዛብህ፣ እንዲሁም ሌሎችን ለመሳደብ ስራ፣ የህዝብ ገንዘብ ከፍለው አሜሪካ ያስመጧቸው ወ/ሮ ንግስት እና አቶ በድሩ አደም ውጪ ወጥተው የፖለቲካ ጥገኝነት መጠየቃቸው የአደባባይ ሚስጥር ሆኗል። እንደሚሰማው ከሆነ እርስዎም አሜሪካ ለመቅረት ካለዎት ፍላጎት በመነሳት፣ በአገር ቤት ያለውን ቅንጅት ለማዳከምና በውጭ አገር እንዳሻዎት ለመፈንጨት እንዲችሉ፣ በቅድሚያ በአገር ቤት ያለውን ኃይል ለመምታት ያደረጉት ጥረት መሆኑን እየሰማን ነው።

እርስዎ የሄዱበት መንገድ የተሳሳተ ቢሆንም፣ አብዛኛው በአገር ቤትና በውጭ የሚገኘው ኢትዮጵያዊ፣ ለቅንጅት ካለው ከፍተኛ አክብሮት የተነሳ ለእርስዎም አስፈላጊውን አክብሮት አልነፈግዎትም ነበር። ሆኖም የምናከብረውን ድርጅታችንና መሪዎቹን በማዋረድ ተግባር ላይ ተሰማርተዋል። በመሆኑም፣ እንደ ሰው ከማክበር ውጪ ቅንጅትን ለመምራት ብቃቱም ሆነ ችሎታው እንደሌለዎት ለማወቅ ችለናልና ከዚህ በኋላ ቅንጣት አክብሮትን፣ በሙስና ከተነካኩት ግለሰቦች እንጂ ከኢትዮጵያ ህዝብ አይጠብቁ... እርምዎትን ያውጡ!

አቶ ኃይሉ ሻወል... ካለፈው ታሪክዎ እንደምንረዳው ከሆነ፣ አቋምዎ በተለያየ ጊዜ ይቀያየራል። "እዬ በጉልበቱ" የመሆን አምባገነናዊ ተግባርዎ፣ አብጦ የሚፈነዳበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ግትርነትዎ ጉድ አሰኝቷል። ቂመኛነትዎ እንደቁስል እያመረቀዘ አልድን አለን። ክህደትና መሰሪነት አይናቸውን አፍጥጠው ከህሊናዎ ውስጥ ቤት ሰሩ። የእርስዎ ጠላት ህዝብና አገርን የሚበድሉት ባለስልጣናት ሳይሆኑ፣ መሪ ብለው የተከተሉት ሰዎች ሆኑ። የእርስዎ ግትር አቋም የሚጠቅመው፣ ህዝብን ሳይሆን፣ በሙስና የተዘፈቁትን እነ ሻለቃ ዮሴፍና ዶ/ር ታዬን ሆነ። የነዚህን ሰዎች ጥፋት ለመሸፈን ሲሉ፣ እራስዎን በዚህ አይነት መልኩ ማዋረድዎና ድርጅታችን ገምት ውስጥ እንዲገባ በማድረግዎ ታሪክ ይቅር የማይለውን በደል ፈጸሙብን። ድርጊትዎም የቅንጅትን ህግ ያልተከተለ፣ ይልቁንም ሻለቃ ዮሴፍ፣ አብረው በነበሩት የቅንጅት አመራር አባላት ላይ የፈጸሙት አይነት ሆነና ብዙዎችን አስደመመ።

ሻለቃ ዮሴፍ ተመሳሳይ እርምጃ በቅንጅት አለም አቀፍ አመራር አባላት ላይ የወሰዱ እለት፣ ማምሻውን በአንድ የዋሺንግተን ሬዲዮ ላይ ቀርበው ሲናገሩ፣ "ይህንን እርምጃ ለመውሰድ በጣም ዘግይተናል። እኔ ወታደር ነበርኩ። ያለነው አሜሪካ ሆኖ እንጂ፣ ሌላ ቦታ ብንሆን ኖሮ፣ ሌላ እርምጃም ይወሰድባቸው ነበር" በማለት በወገኖቻቸው ላይ ግዳያ ሊፈጽሙ እንደሚችሉ አውጀው ነበር። ነገሩን ስናስበው እርስዎም በተመሳሳይ መልኩ፣ "እኔ የደርግ ባለስልጣን ነበርኩ። የጊዜ ጉዳይ

በጎልማሳነት ዘመንዎ፤ ልጆችዎን ለማሳደግ ሲሉ ኢትዮጵያን ለማገልገል ሳይፈልጉ ቀሩ። ለመሆኑ ዛሬ ሌሎቹ የቅንጅት አመራር አባላት የሚያሳድጉዋቸው ልጆች ሳይኖሩ ቀርተው ይመስልዎታል ትግል ውስጥ የገቡት?" መልሱን ለርስዎ ልተወውና ወደቁምነገሬ ልመለስ።

እንደ እውነቱ ከሆነ፤ ከምርጫ 97 በኋላ፤ የተገኘውን ድል በመያዝ ወደ ፓርላማ በመግባት፤ አዲስ አበባንም ሙሉ ለሙሉ መቆጣጠር ይቻል ነበር። በወቅቱ የቅንጅት ላዕላይ ምክር ቤት አዲስ አበባንና ፓርላማውን ለመቆጣጠር፤ በሙሉ ድምጽ የወሰነ ቢሆንም፤ "እንዴት አዲስ አበባ ለዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ይሰጣል?" ከሚልና የሌላ ፓርቲ ሰዎች በብዛት አሸንፈው ለፓርላማ በመብቃታቸው፤ ካደረብዎት ሰይጣናዊ ቅናት በመነሳት፤ የላዕላይ ምክር ቤቱ የደረሰበትን ውሳኔ ለመቃወምና ለመጥፎ ተልዕኮዎ ሲሉ ህክምናዎን አቋርጠው አዲስ አበባ ተመለሱ።

አዲስ አበባ ተመልሰው መሰሪ ሃሳብዎን ሲያቀርቡ፤ ብሎም ላዕላይ ምክር ቤቱ ሃሳብዎትን ካልተቀበለ፤ ድርጅቱን ለቀው እንደሚወጡ በስብሰባ ላይ አስፈራሩ። እንዲያውም ከአንዴም ሁለቴ ስብሰባውን አቋርጠው ሊወጡ ሲሉ፤ በነኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው ልመና ወደ ስብሰባው መመለስዎ ይታወሳል። በወቅቱ በቅንጅት መካከል መከፋፈል እንዳይፈጠር በመስጋት፤ ብዙዎች የእርስዎን ሃሳብ በግማሽ ልብ ደገፉ። ከአንድ የፖለቲካ ድርጅት በማይጠበቅም ሁኔታ፤ መመሪያ ከመስጠት ይልቅ ከህዝቡ መመሪያ ለመቀበል በአገር ቤት ስብሰባዎች ተጠሩ። በውጭ አገር ደግሞ፤ ህዝቡ በወያኔ ድርጊት ከመናደዱ ብዛት፤ "ፓርላማ እንዳትገቡ" የሚለው ሃሳብ እያየለ መጣ።

እናም ላዕላይ ምክር ቤቱ አስቀድሞ ወስኖት የነበረው ሃሳብ ተሽሮ፤ በገባንበት አረንቋ ውስጥ እንድንዳክር ተገደድን። ነገሩ የድርጅት ውሳኔ በመሆኑ ባንፈልገውም አላማውን የማሳካት ግዴታ ስለነበረብን ጉዳዩን በደምሳሳው ተቀብለን፤ ከጋኔናዊ ወያኔ ጋር እልህ አስጨራሽ ትግል ውስጥ እንድንገባ ሆነ። ከዚያም ጋር በተያያዘ በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን ለእስርና ለስደት ተዳረጉ። ታዲያ ለዚህ ሁሉ ደም ተጠያቂ የሚሆኑት እርስዎና መለስ ዜናዊ እንጂ ሌላ መሪ ሊሆን አይችልም።

ትላንት ከትላንት ወዲያ በነጭ ሽብርና ቀይ ሽብር አማካኝነት ለጠፋው ህይወት፤ ኮ/ል መንግስቱ ኃይለማርያምና ኢህአፓ ተጠያቂዎች እንደመሆናቸው ሁሉ፤ በቅርቡ ለሆነው ጥፋት ሁሉ ደግሞ መለስ ዜናዊና ኃይሉ ሻወል በእኩል ደረጃ ተጠያቂ መሆናቸው የማይቀር ነው።

ይህ ሁሉ እንግልት፣ ሞት፣ እስራትና ስደት የተከሰተው እርስዎ በሰጡት አመራር ምክንያት መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። እንደ እውነቱ ከሆነ፤ የቅንጅት ደጋፊዎች ለዚህ መስዋዕትነት የተዳረጉት ለግለሰቦች ልዕልና ሳይሆን፤ ለአገራቸውና ቅንጅት ለያዘው አላማ መሆኑን ደግመን ደጋግመን ማሰብ ያስፈልጋል። አቶ ኃይሉ ሻወል ግን በነዚህ ለጋ ወጣቶች ሞት ሁለት ጊዜ ነግደውባቸዋል። በመጀመሪያ የቅንጅት የልዑካን ቡድን ወደ አሜሪካና አውሮፓ በሄዱበት ወቅት፤ በነሻለቃ ዮሴፍ ያዘው በኩል የደም ገንዘብ እንዲላክልዎ አድርገው፤ ከሃያ በላይ ለሚሆኑ ቤተሰቦች ለያንዳንዳቸው፤ "1ሺህ አምስት መቶ ብር" ($200 የአሜሪካ ዶላር) ሰጧቸው። በእውነቱ ገንዘብ መስጠቱ አልከፋም፤ ነገር ግን አሰጣጡ ነው ቅር የሚያሰኘን።

በወቅቱ የልዑካን ቡድኑ ከመሄዱ በፊት ለስብሰባ ሲጠራዎ "በህመም ምክንያት" ለመገኘት ሳይችሉ ቀርተው፤ የልዑካን ቡድኑ አዲስ አበባን ለቅቆ እስከሚሄድ ጠብቀው፤ እርስዎ ብቻዎን በየሰፈሩ እየሄዱ እርጥባን ለመስጠት ጊዜ ማግኘትዎ ያስገርማል። አሁንም ገንዘብ መስጠቱ አያስከፋንም። ገንዘቡን ከራስዎ ኪስ አውጥተው የሰጡ ማስመሰልዎ ግን ይገርማል። ክብርዎን የሚነካ ስለመሰልዎ እንጂ "በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን የላኩላችሁ ነው፤" ማለት ይችሉ ነበር። ነገር ግን የርስዎ አላማ፤ በውጭ ያሉ ኢትዮጵያዊያን ያዋጡትን ገንዘብ በመስጠት፤ ተራ የግል ዝና ማግኘት ስለነበር፤ በእርጥባን ስም በለጋ ህጻናቶች ደም ነገዱ። ከልብ የሚያዝኑ ቢሆንማ ኖሮ፤ ምነው ፕሮፌሰር አስራትን፤ "እግዜር ይማርዎ ወይም ይግደልዎ" ማለት ማንን

ሆኖ እንጂ…" የሚሉ እየመሰለን መጥቷል። እንግዲህ እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ስለሚወዳትና ስለሚጠብቃትም ይሆናል፤ እርስዎን በስልጣን ላይ ያላስቀመጥዎ።

በአጠቃላይ ድርጊትዎ ሁሉ፤ ትላንት ከፍተኛ መስዋዕትነት የተከፈለበትን የአገር ጉዳይ የዘነጉ አስመስሎታል። ህዝቡን ንቀውታል። አልፎ ተርፎም በህዝብ ትግል ላይ በማላገጥ፤ ህጻን ልጅ የማይፈጽመውን አስነዋሪ ተግባር በድርጅት ላይ በመፈፀም ላይ ይገኛሉ። ለመጪው ትውልድ መልካም ነገርን ከማውረስ ይልቅ፤ እኩይ ድርጊትን አወረሱት። የትም በማያደርስ ተግባርዎ በመግፋት፤ ይበልጥ በህዝብ ዘንድ እንዲጠሉ የሚያደርግዎትን፤ "ያዋጣኛል" ያሉትን መንገድ ጀምረዋል። እኛ ግን አላማችንና ግባችንን አስተካክለን በሰላማዊ መንገድ ትግላችንን እንቀጥላለን።

እርግጥ ነው፤ ከዚህ በኋላ ከፍተኛ ስራ ከፊታችን ይጠብቀናል። እርስዎ እስከዛሬ የተከፈለውን መስዋዕትነት በዜሮ በማባዛት በባዶ ሊያስቀሩት ሞከሩ፤ ግን አልተሳካም። እርስዎ አጠፉ ብለን እጃችንን አጣምረን አንቀመጥም። በኛ በኩል የምንፈጽማቸው ቁምነገሮች ይኖሩናል። አዎ… ይህንን ክፍፍል ተቃራኒ ወገኖች እንዳይጠቀሙበት፤ ጥንቃቄ በማድረግ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ የሚደረገውን ትግል እንገፋበታለን። ለእውነትና ለሃቅ ከቆሙት ጋር ሰልፋችንን አስተካክለን ወደፊት እንራመዳለን።

ከዚያ በተረፈ ግን፤ ቀደም ተብሎ እንደተገለጸው፤ እርስዎ በታሪክ አጋጣሚ የቅንጅት ሊቀ መንበር በመሆንዎ የድሮውን ነገር ወደ ኋላ በመተው፤ አስፈላጊውን ክብር ስንሰጥዎ ቆይተናል። አሁን ግን ህዝብ በደሙ እና በህይወቱ የከፈለውን ዋጋ፤ የቅጥፈትና የክህደትን ካባ በመደረብ ሊያጨናግፉት ጥረት በማድረግዎ፤ የሰጠንዎትን ክብር ስለህዝብ እንባና ደም ስንል አንስተነዋል። ያለንን ክብር ማንሳት ብቻም ሳይሆን፤ ከእንግዲህ በኋላ፤ ህዝቡንና ድርጅቱን በግልፅ ይቅርታ የማይጠይቁ ከሆነ፤ እንደሊቀ መንበር የማንቀበልዎ መሆኑን በታላቅ ትህትና እንገልጽልዎታለን።

ይህን የምንገልጽልዎትም፤ ከእንግዲህ ወዲህ እርስዎን የምሸከምበት ጫንቃ ስለሌለን ነው። ከዚያ ውጪ ለሃቅ የቆሙ ኢትዮጵያዊያን ለግለሰቦችና ለቡድኖች አያጎበድዱም፤ አያመልኳቸውምም።

ከዚህ በኋላ ትግሉ ሁለት መንገድ ይዟል። አንደኛው በቅንጅት ስርአትና ደንብ መገዛት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከአምባገነኖች ጋር አብሮ መሄድ። አቶ ኃይሉ ሻወልና ተከታዮቻቸው የተከተሉት ሁለተኛውን ምርጫ ነው። በሁለተኛው መንገድ እርስዎና ወዳጆችዎ ትጓዛላችሁ… መንገዳችሁም በአምባገነን የሚመራ በመሆኑ፤ በጉዟችሁ መሃል እርስ በርሳችሁ መበላላታችሁ የማይቀር በመሆኑ፤ መንገዱን ጨርቅ ያርግላችሁ ከማለት ሌላ የምንለው ነገር አይኖርም። በኛ በኩል ምርጫችንም ግልፅ ነው። ለዴሞክራሲ የቆምን ወገኖች፤ ከዲሞክራሲያዊ ሃይሎች ጋር እንጓዛለን። አሁን መንገዳችን ግልጽና የጠራ በመሆኑ፤ ትልቅ ጫናም ከላያችን ላይ ስለወረደ፤ ያለ ችግር ወደፊት እንገሰግሳለን። የኢትዮጵያም ህዝብ ሰላማዊ ትግል የሚያካሂዱትን ዲሞክራሲያዊ ኃይሎችን ይከተላል።

አንድ የመጨረሻ ነገር ለመግለጽ ይፈቀድልን። በቃሊቲ እስር ቤትም ሆነ ከዚያ ውጪ መከራን ያሳለፉ ቅንጅታዊያን፤ በእርስዎ አካሄድ ፍፁም አይረበሹም። እንኳንስ ለዚህ ቀርቶ ህይወታቸውን ለመስጠት ተዘጋጅተው የነበሩ ሰዎች ናቸውና። የቅንጅት ደጋፊዎችም በተገቢው ሁኔታ በእሳት ተፈትነዋልና ለአላማቸው በፅናት ይቆማሉ፤ ለህዝብ ክብር ለሚሰጡ መሪዎችም አስፈላጊው ኢትዮጵያዊ ክብር ይለገሳቸዋል። ሰላማዊ ትግላችንም በፅናትና በጥራት ይቀጥላል። የህይወትና የደም ዋጋ የከፈሉ ኢትዮጵያዊያንም ውለታም፤ በኃይሉ ሻወልና ተከታዮቹ አይጠፉም። ይልቁንም ከመቃብራቸው በላይ የዲሞክራሲ ቡቃያ ያብባል።

የኢትዮጵያ አምላክ አገራችንን ይጠብቃት!